# ደሞ ለሴት!? የአገር ክህደት አንድምታው – አሰፋ ጫቦ

December 2, 2015 -

አሰፋ ጫቦ Dallas Texas USA

የዛሬው እናቴ፤ማቱኬ አጆ ፤ስትል የነበረውን አስታወሰኝ።"ወሐውን ማን ያናግረዋል **?** ድንጋይ**!** ድንጋዩን ማን ያናግረዋል**?** ውሐ**! "**ትላለች**!** ስትል ነበር**!** በተፈጥሮም ሆነ በሰዎች ሕይወት ወስጥ ያለዉን የመነካካት፤የመያያዝ፤የመተሳሰር አንዱ ሌላውን የመቀሰቀስ **(Chain Reaction)** ነገር ለመግለጽ መሆኑ ነዉ። ዛሬ በዋናነትና ፤በብቸኝነት ለማንሳት የፈልግሁት የኢትቶጵያ የስፓርት ፌደረሽን በቁሙ ስለቀበረው የኢትዮጵያ የሴቶች የእግአገር ኳስ ቡድን ነበር።

የመነካካቱ ነገር ያመጣውን የወደዚያ ጉዞ መንገድ ለማሳየት ስፈልግ ደግሞ ረዘመ፣ተራዘመ**!**መቻልነው ደጉ**!** ሸገር ራዲዮ **FM 102.2** ድንገት **Facebook** ላይ አገኘሁትና አዳመጥኩት።የዳመጥኩትን ደግሞ በአብዛኛው ወደድኩት።የመአዛ ብሩ ቃና፤መአዛ ነበረው።መአዛን **2001** ይሁን **2002** ነው ዮርክ **(New York,NY)**ወርጄ ለ **4** ይሁን **5** ስአት አነጋግሪያት ነበር። ወርጄ ማለቴ ያኔ የነበርኩት ኬምብርጅ ፤ማሳቹሰትስ **(Cambridge,Massachussets)**ነበርና ነው። አነጋገርኳት ከማለት ይልቅ አናዘዘችኝ **(**ሌላችንም እንደምታደረገው**)** ማለቱ ሳይሻል አይቀርም።ለራዲዮ መሆኑ ነው። ሸገር የሚባል ራዲዮ መኖሩን ያኔ አላውቅም ነበር። የሰው አገር ሰው ነገር**!!** መአዛ ብሩን ያኔ ገና ሳያት ወደድኳት።የሐረርጌ ሰው መሆንዋን ሁለንተናዋ ይናገራል። **"**እንኳን ደህና መጣህ**!"** የሚል መልእክት**(Body Language)** ያለው ይመስላል። አሁንማ በሸገር **"**አሻም**!!"** ስትልም ሰማሁ።እንደኛው እንደጋሞዎቹ መሆኑ ነው።አሻም**!!**እንኳንደህና መጡ**/**ሽ**/**ህ መሠረታዊ ትርጉሙ ይሆንና የጋሞዉ ተጨማሪ እቅፍ የማድረግ ጠረን፤ቃና፤ቅባት ያለው ይመሰለኛል**።**

የመአዛ ነገር ሌላዋን የማውቃትን፤ቤትዋም ለመሔድ ዕድል የገጠመኝን ትዝታ በላቸውን አስታወሰኝ።ሌላው ተመሳስይነታቸው እንደተጠበቀ ሁኖ በመልክም የሚመሳሰሉ እንኳ ባልል የሚቀራረቡ መሰለኝ።ትዝታ በመጠኑ ቀጠን፤ትንሽም ረዘም ሳትል የምትቀር አይመስለኝም። ትዝታን አምና በመጋቢት ወዳጄ በነበረው ሙሉጌታ ኃይሉ መታሰቢያና መዘከሪያ ስበሰባ ላይ **Washington D.C** አግንቻት በደንብ ሳንጨዋወት ተለያየን። መአዛ ብሩና ትዝታ በላቸው የሴት የራዲዮ አቅራቢና ፈረ**-**ቀዳጅ የነበረችውን ሮማነ ወርቅ ካሳሁንን ያስታውሱልኛል። ሮማነ ወርቅና መጀመሪያ ያደመጥኳት ልጅ ሆኜ ጨንቻ ነበር። የ**"**ገሙ**"** አውራጃ ግዛት ዋና ጸሐፊ የነበሩት አቶ አስፋ ዳዲ መኖሪያቸው ፊታውራሪ ሳጌ ሜንዴ ፎቅ ላይ ሁኖ ስምንት ሰአት ሲሆን ደርጃው ላይ ያወጡትና ራዲዮናቸውን ይከፈቱ ነበር።።በከተማው ያለው ብቸው ራዲዮ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ሮማነ ውርቅ አሁን ካለችበት ወዲያ ማዶ፤ከጽራሐ አርያም ሁና መአዛንና ትዝታ **"**አርማዬን ደህና አድርጋችህ አንስታችኋል**!!** ግፉበት**!!"** የምትል ይመስለኛል። ሸገር ላይ ካደማጥኩት **3** ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያውና ለየት የሚለው አቡነ ብርሐነ እየሱስ ሱራፌልና መአዛ ያደርጉት ውይይት ነበር። መወያየት ሳይሆን መጨዋወት ብለው ይሻለኛል**!**የማልረሰው ዘላቂ መሕተም ያተሙብኝ ይመስለኛል።በዚያ ላይ ሁለቱም ሐረርጌዎች ናቸው።ምን ማለቴ እንደሆነ የሐረርጌን ሰው የሚያውቅ የበለጠ ይረዳኛል። ጫወታው ሳይዳልጠው እንዳለ የሚወርድ ነበር። ሊቀ ጳጳስ ብርሐነ እየሱስ አኮሩኝ**!** ኢትዮጵያን የካርዲናል **(Cardinal)**አገር አስደርጓት**!** በዚህ ላይ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአካባቢ አገሮችም ጳጳስ ናቸው።ስለካቶሊ ካርዲናል፤ሊቀ ጳጳስ፣በቅጡ ለማናወቅ ፤ከቤተክርስቲያኒቱ ጳትሪያርክ፤ **(**ፖፕ **Pope)** ለጥቆ ያለው መንበር ነው።ካርዲናሎቹ ፖፑን መራጮችም በተራቸው ሊዚያ መንበር ተመራጮችም ናቸው። ካርዲናል ብርሐነ እየሱስ ነገ ተመርጠው በቅዱስ ጴጥሮስ መነበር ላይ ሲቀመጡ ይታየኛል**!**እንዲያዎም **"**የፈረንጅ፤በተለይም የጣሊያን ተወላጅ ፖፕ ዘንተ ዓለም ነገሠበት**"** የሚል ሮሮ ስለነበር ነዉ የአሁኑን አርጂንቲና ወረደው የመርጡት በዚህ ምክንያት ጭምር ነው የሚል በሰፊው ተጽፎ ሳነብ ስንብቻለሁ።የሚቀጥለው ዙር የአፍሪቃ፤ ከሆነም የኢትዮጵያ እንደሚሆን እመነትም፤ተስፋም፤ምኞትም አለኝ። **"**ቸር ተመኝ**!** ቸር እንድታገኝ**!"** ነውና። እኚህ ካርዲናል ብርሐነ እየሱስ ተዘዉትሮ የምናውቀው ጳጳስ አይነትም አይደሉም።ዉጣ ውርደቻው ከኔው፤የኔው ትውልድ የተጓዘበት ወጣ**-**ገባ አቀበት፤ቁልቁለትና ገደላ**-**ገደል አቋቆራርጦታል።ዩኒቨርስቲውም አንድ ዘመን፤የተማሪ ንቃናቄውንም ደርግንም ከነመራራውና ኮምጣጣው ጎኑ ተጎምጭተዋል። በዚያ ጎራ አልፈው ወሬ ነጋሪ ከተርፍነው ውስጥ ናቸው። ሸገር **FM 102.2** ጎራ ብሎ ማዳማጥ ነው። አሜሪካ ያላችህ ስልክ ቁጥር **712 432 6885** ደውሎ ማዳማጥ ይቻላል።ካልተገኘ አርካይብ **(**የትላትን ማሕደር**)** የት እንደሚገኝ መአዛን መጠይቅ ነው። እኔማ ሲለኝ አንድ ቀን ስለ እኚህ ጳጳስ መጻፌ የማይቀረ ይመስለኛል። ስለጳጳሳት የመጻፍ ልምዱም አለኝ። ስለ አቡነ ጳውሎስም ስለ አሁንም ፓትሪያርክ አቡነ ማቲያስ ጽፊያለሁና**!** ሁለተኛ ያደመጥኩት የዘፋኟን የጸደነይን መልልስ ነበር።በየትኛው እንደሆነ እንጃ እንጅ አንዴ በተለቪዥን ቃል ምልልስ ስታደርግ አድምጭያት ነበር።ስምዋ ያለተመደ እሷ ደግሞ አውቄ የኖርኳት አይነት ሆነችብኝ።እንደዘፋኝ፤እንደታዋቂ ዘፋኝ ሳይሆን አነጋገርዋ ልክ እንደኛው እንደተራና ተርታ ሰዎች ነበር። ለአደባባይ ያዘጋችው ገጸ ባሕርይ**(Public Persona)** አልነበራትም።የማእከላዊ ወዳጄ የነበረውን ጥላሁን ገሠሠን አስታወሰችኝ።ጥላሁን በአካልሲያዩት፤ሲያነጋግሩት በዝና ስማየ ሰማየት፤አጽናፈ አጽናፋት የነካ፤የነገሰ ፍጹም አይመስልም።

መምስል ሳይሆን መሆንም ስለነበር ትንሽ ለማመን የሚያስቸግር ነበር።**"**እርግጥ አንተ ያ ያ ጥላሁን ነህ**!?"** ብል በል የሚያሰኝ ነገር ነበረው

ጸደነይ በአፍሪቃ የዘፈን ውድድር ናይጀሪያ ወርዳ፤ዘፍና፤አምራ- ሠምራ ፤የለበሰችው ጥበበ ፤ (እድሜ ኑሯቸው "ያው በገሌ!" ለሆነ ጋሞ፤ዶርዜ ዘመዶቻቻችን ይስጣቸውና)፤የጉድ- ጉድ ተደንቆ ፤በዚያም ላይ አሸንፋ አሁን ጥዋት አዲሳባ ስትደርስ ከእንቅልፏ ቀድሞ ሸገር አግኝቷት የሰጠችው ቃለ ምልልስ ነበር ያደምጥኩት።ባቡር ዉስጥ በጆሮ ማድመጫ እያደምጥኩ ነበርና ስትጨርስ "እስይ አበጀሽ የኛ ሸጋ!ባሳር ተገሽ በፍልጋ !" አልኩኝ ጎላ ባለ ድምጽ።"What did you say now?" አለችን ከጎኔ ተተቀመጠችው ፈርንጅ። "ምን አልከኝ አሁን?" ለማለት ነበር። (Thinking out Loud!"አልኳት። "ብቻዬን እየውጠነጠንኩ ነኝ!" ለማለት።እዚህ ለብቻ መናገር እንደልብ ነውና አልገርማትም። እንዳልኩት ይህ ሁሉ ወደተንሳሁበት መግቢያ መሆኑ ነው! 3 ኛ ያደመጥኩት የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴረሽን የሰጠውን ቃለ መጠይቅ፤ ወይም በዚያ ቃለ መጠይቅ ላይ የተሰጠውን ፍሬ ሐሳብና ግምገማ ነበር።የኢትዮጵያ ስፓርት ፌደረሽንር፤ አውቆ በድፍርትና በንቀት፤ ያለበለዚያም በንሕዝላልነት፤በማን አለብኝነት፤"ደሞ ለሴት የኳስ ቡድን ያን ያክለ ስፍራ ቦታ መሰጠት !!"በሚል በቁሙ የቀበርበትን ታሪክ ነበር።ታሪክ ሳይሆን ደረቅ አይን ያወጣ ወንጀል ማለቱ ይቅል መስለኝ።ለኔ! ገረመኝ! ደነቀኝ! የሰማሁትን ማመን አቃተኝ! ደግሞም የተወሳሰበ ነገር፤ነጥብ(Issues) አልነበረውም! የኢትዮጵያ የሴቶች የእገር ኳስ ቡድን፤በአፍሪቃ የሚያሸንፈውን ሁሉ አሸንፎ ለሚቀጥለው ለመጨረሻው ውድድር ሊሔድ ተዘጋጅቷል።አዘጋጆቹ ፤የአፍሪቃ ስፖርት የበላይ አካላት፤ " ጎበዝ! እንግዲህ መቼ ነው የምትመጡት?" የሚል ደብዳቤ ለኢትዮጵያው ፌደረሽን ይልካሉ።መልስ የለም!! ትንሽ ቆየት ብለው ሁለተኛ ደብዳቤ ይልካሉ።

አሁንም መልስ የለም! "ጎበዝ !አገር ደህና !?"በሚል ሶስተኛም ደብዳቤ! ጭጭ! አራተኛም ደብዳቤ ይላካል! ፍንክች ያባቢለዋ ልጅ !! እንደገናም ዝም! ጭጭ ! ምጭጭ! ሆነ:: አካሉ የማታ የማታ የብረት መዝጊያውን ቀርቅሮ፤መክፍቻውን ቁልፍ ወረወረው!!የኢትዮይዮጵያ ሴቶች ልጆች፤እንደጸደነይ ፤አደባባይ ውለው ፤አምረው ሠምረው፣ ዋንጫ አንግተው፤ጎሮ ወሾባይ ፤ "አለምሽ ዛሬ ነው ዛሬ!ኢትዮጵያ አገሬ!" ብለው እየዘመሩ፤እየፎከሩ፤እያቅራሩ የሚመጡበትን የተሰፋ ምድር የስፖርት ፌዴሬሽን በቁሙ ቀበረው።ማቅ ም አለበበሰው! ጥላሸትም ቀባው!! የስፖርት ፌዴረሽን ጋዜጣው መግለጫ ለመስጠት የግዱን የተስማማው ይህ ፤ብሔራዊ የቀበር ሥነ ስረዐት እንዴት እንደተፈጸመ፤ማን ጉድጓድ ቆፋሪ፤ማን አፈር አልባሽ፤እንዴት?ለምን? መቸ? የሚለውን ለማስረዳት ነበር የግዱን የተስማማው።የግዱን የሚያሰኘው የመጀመሪያው ደብዳቤ የመጣው በሰኔ ወይም ከዚያ በፊት ሁኖ የመጨረሻው የመጣው በነሐሴ ወር ነበር።አምና ማለት ነው። የጋዜጣ መግለጫው ደግሞ ዘንድሮ በሕዳር ወር ነበር::ጋዜጣዊ መገለጫው ወይም ፍሬ ነገሩንና (ፍሬ ነገር ቢኖረው) ትንተናውን ሳዳምጠው የበለጠ ገረመኝ። እንደምናውቀው የኢቶትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 90 ሚሊዮን ነው። ሴት- ወንድ ስብጥሩ መሳ- ለመሳ (50%)ነው። ማለትም ኢትዮጵያ 45 ሚሊዮን ሴቶች አሏት ማለት ነው። የኢትዮጵያ ስፖርት ቦርድ ውስጥ አንድ ሴት እንኳን የለበትም ። በፌዴረሽኑ ውስጥ የሴቶች ጉዳይ ሐላፊ ደግሞ አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ ናቸው። አቶ ወንድ መሆናቸውን አንጠራጠርም። ወይም ሴት አለመሆናቸውን እርግጠኞች ነን። ይህም ማለት ከዚህ 45 ሚሊዮን ሴት ውስጥ ለዚህ ለቦርድ የሚበቃ፤ሌላው ቢቀር የሴቶችን ጉዳይ የሚትከታተል አንዲት ሴት ማገኘት አልተቻለም ማለት ነው። ወይም፤ ለመሆኑ ይህ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴረሽን በየትኛው ምዕተ አመት ውስጥ ነው የሚገኘው?ማለትም ተገቢ ጥያቄ ይመስለኛል። ተራ፤የታወቀውና የተለመደው የወንድ ትምክህተኝነት ብሎ ለማለፍ ትንሽ የሚከብድ ይመስለኛል።እኔ የከብደኛል!! ዘመን መሳፍንት የሚባለው መቼ ነበር?200 መቶ አመት አለፈው?ያም ዘመን ቢሆን እንደነ ዕቴጌ ጣይቱን መሳይ አፍርቶ ነበር። ይህ አገር ዛሬም የነጣይቱ አገር ነው!! እንዚህ የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ዘመናቸው የፈቀደውን ጀግንነት አድዋ መዝመታቸው ነበር። ሌላው የህን የተስረውን ደባ፤ኩነኔ ለማካካስ ተወሰደ የተባለው እርምጃ የበለጠ ደነቀኝ።አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ፤የሴቶቹ ተጠሪ፤ ከስራቸው ተጋዱ። ዮሴፍ፤የሴቶች ኃላፉዉ ታገዱ! ኃላፊ ያልነበሩ፤ወረድ ብለው ያሉ ፣ ግና ሴት የሆኑ ፤ከስራቸው ተባረሩ! ለማማን የሚያስቸግር ቢመስልም የነገሩን ይህንኑ ነበርና እውነቱ መሆኑ ነው! ተባለ! "እሰየዉ! የምንላከክባት ሴት ተገኘች!" መሆኑ መሰለኝ:: ነውም ! "ጉድ ሳይሰሙ መስከረም አይጠባም!" ይባል የለ ? አንዴ እስቲ ቆይ! Just a Minute! "...ከንፈረ ሞንሟና ከዚሁ ተስሞ ምን ይተርፋትና "ም ይባል ይለ ? እኝህ ፥ከስራቸው ታገዱ የተባሉት ፤አቶ ዮሴፍ፤ ተናገሩ የተባለውን Facebook ላይ ያገኘሁትን እንደወረደ እዚሁ ለጠፍኩት። እንዲህ ም አሉ። "ህዝቡንም...ሚዲያውንም ለማብረድ አንተ ጥፋተኛ ነኝ ብለህ ይቅርታ ጠይቅ...እኛ ከሁለት ሳምንት በኋላ እንመልስሃለን ብለውኛል።" .... አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ ከእግር ኳሥ ፌዴሬሽኑ ታግደዋል የተባሉት አመራር ..ሂልተን ሆቴል በግል በሰጡት መግለጫ የተናገሩት" እኔ ይህንን አምናለሁ! ኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴረሽን፤በዚህ የሴቶች የእግር ኳስ ዙሪያ ያደረገውን Page 4 of 5 ትልቁን ምስል ስምለከት ፤እንደ "የአካባቢ ማስረጃ (Circumistentioal Evidence)ወስጄ ካለማመን ወደማመማኑ አዘንብላለሁ።ካልሆነ ደግሞ አላልኩም ብለው ማስተባበሉ የአቶ ዮሴፍ ፋንታ ነው።

እናም፤ይኸ፤የወንዶች የኢትዮጵያ የስፖርት ፌዴረሽን ስራ የኖርወይ (Norway)3 ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩ፤ በኋላም የአለም የጤጥ ጥበቃ (WHO)ዲሬክተር ይሆኑት Gro Hartlem Brutland ተነገሩ የተባለውን አስታወሰኝ። አንዴ ጠቅላይ ሚኒስተር የሆኑ ጊዜ ካቢኔያቸውን፤ሚኒስትሮቻቸውን በሙሉ ሴቶች ብቻ ሾሙ። "ምነው ምነው ወንድ በአገሩ የለም ወይ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው "የወንዶችን ስራ እስከዛሬ አይነዉኮ !"አሉ። "አለምን እዚህ ማጥ ውስጥ ለዘመናት የዘፈቁ ወንዶች አይደሉም ወይ?" አሉ። መልሳቸው አጉል አባባል አስታወሰኝ።"ለማይውቅሽ ታ..." የሚለውን ።ታዲያ፤ይኸ የስፖርት ፌዴሬሽን ስራ Bruntland ያሉትን ሸተተኝ። እኔ የማቱኬ አጆ ልጅ ነኝ።ከለስላሳውና ልዝቡ አባቴ ይልቅ ሁለንተናዬ በናቴ የወጣ ይመስለኛል።አንዴ፤እዚህ አገር የመሐል ስም (Middle Name)የሚሉትን ጨምሬ አስፋ ማቱኬ ጫቦ መባል አለብኝ የሚል መጣብኝና ህጋዊ ለማድረግ ፍልጌ ፍርድ ቤት ሄድኩ። "ችግር የለም!" ብላ የሚሞላ ቅጽ(form) ሰጠችኝ። ቅጹን ሞልቼ ስመልስላት ደረሰኝ ለመቁረጥ ተዘጋጅታ "$200 አምጣ!" አለችኝ። እናቴንስ በ$200 አልለውጥም ብዬ ተውኩት። ማቱኬ ሰውን ሁሉ፤ወዳጅ፤ወዳጅ ያለሆነ፤ዘመድ አዝማድ፣ወንድሴት፣ልጆቿን ጨመሮ የምትከፍለው በሁለት ብቻ ነበር።

ሥነስር አት ያለውን ሥነ ስረ አት የሌለው።ሥነ ስርአረት የለውም ለምትለው የምትጠቀመውን ቃላት እዚህ መድገም አልፈልግምም።ከበድ ይላል። ደርግ ሁለት ልጆቿን አስሮ ነበር።የኔ መታሰር ተደብቆ ኖሮ ሲሰለቻት "አዲሳባ ሄጄ ማየት አለብኝ !" ብላ ተነሳች።ምርጫ ሲታጣ "ታስሯል!" ሲሏት "የኔን ልጆች እያሳደደ የሚያስር አሳዳጊ የበደለው ባለጌ ማነው!?" ስትል መንግስቱ ኃይለማርያም መሆኑን ንገሯት። መንግስቱን ለማነጋገር በነጋታው ተነስታ አዲሳባ መጣች። አንጋገርችውም! እንዴት አድርጋ እዚያ እንደደረሰች የገርመኛል።

ዝርዝሩን አልነገሩኝምና ነው። የሆነ ሆኖ የመንግስቱ ጠባቂዎች ትንሽ አጉላልተዋት ስለልነበር፣ለነሱ፣ለራሳቸዉ፣ ስለነሱ የምታስበውንም እዚያው ነገረቻቸው አሉኝ። ይህንን ማምጣቴ መሆን የሚገባው ሳይሆን ቀርቶ ፤መሆን የማይገባው ሲሆን ፤ማለትም ሥነ ስርአት የጎደለው ሆኖ ሲገኝ፣እኔንም እንደእናቴ ያደርገኛል ለማለት ነው። የዚህ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን ድርጊት እንደዚያ አደረገኝ!! በመሠረቱ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴረሽን መባሉም ትክክለኛ ስሙ አይመስለኝም።የወንዶች ፌዴረሽን ቢባል እርግጠኛና እውነተኛ ስሙ ይሆነልና።

የሚወክለው ከኢትዮጵያ ሕዝብም ውስጥ ከፊሉን **(50% )**ነውና።ደግሞም ይህ በሴቶች የእግር ኳስ ቡድን ላይ የተፈጸመው ደባ የአስራር ቸልተኝነት፤ መሪ የማጣት ችግር አይመለኝም። ብቻ አይመስለኝም! መሠረታዊ የሰው ልጆች የሙብት ገፈፋ ጥያቄ ነው። አገላባብጩ አላየሁትም እንጅ፤ሌላ ቦታ እንዳልኩት የደረቅ ወንጅልነትም ባሕርይ አያጣም።

በኔ አስተያየት የዚህ አይነት ድርጊት እንዳይደገም ፤መቀጣጫም ፤መማማሪያም እንዲሆን ከስር መሠረቱ መስተካከል ያለበት ይመስለኛል። ይህ እንዴት ነው የሚቻለው ? ለዚህ ዛሬ ምን ችግር አለው! ትላንትና የኢትዮጵያ መንግስት፤ ኢሕህአደግ ፤በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት "እዚህ ቤት ጉዳ ፍልቷል!" ብሎ ያለ የሌለ ጉዱን በአደባባይ ነግሮን የለ! ስለዚህም በመላው ኢትዮጵያ ያሉት የሴቶች ማህበራት፤የሰብአዊ ሙብት ተቋማት ፤የፌዴረሹን አባላትና አካላት የሆኑ ቡድኖች በሙሉ በሚመቻቸው መንገድ ሁሉ**(By all Means Necessary)** ተነሰተው ፌዴረሹኑን ካለበት ጽኑ ሕመም አጽድተው እውነተኛውንና የሚወክለን ፌዴረሽን መቋቋም ማለት ነው። በሌላ አነጋገር የጽዳት ዘመቻ ማካሄድ ማለት ነው። መመንጠር ሳይሆን ማጽዳት ማለት ነው። እድሜ ለዘመኑማሕበራዊ ድሕረገጻት **Social Media)**አሉልን! ሆይ ብዬ መጣሁ ሆ ብዬ ! የአፍሪቃ ዋንጫ ይገፑ! ሆይ ብዬ መጣሁ ብዬ ሆ ብዬ !እያሉ የሴት ቡዳንችን ሲገባ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች፤በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተስፈኛ ፤ታዳጊ ወጣት ሴቶች ሲቻል በአደባባይ፤ሳይሆንም በሒልናቸው፤በየመንፈሳቸው እ-ል-ል-ል-ል-ል-ል-ል! እያሉ የሚቀበሉበትን ቀን ለመፈጠር ነው። አገር ሲከዳ ለማየት የግድ በአደባባይ ጃን ሜዳን ለፈረንጅ የሚያስማማ እጅ ከፍንጅ መያዝ ያለብን አይመስለኝም። አገር መክዳት ብዙ መልክና አንድምታም አለው ብዬ አምናለሁ፡-

የጸዳ ቤት ለማየት ያብቃን!! የከርሞ ሰው ይበለን!!